# ምድብ ሁለት (ከ1ኛ — 3ኛ) ክፍል

## 25 ኛ ሳምንት

## ኒቆዲሞስ

***ዓላማ***

- ከኒቆዲሞስ ሕይወት መማር

***ምንባብ***

- ዮሐ. 3÷1-15

***መግቢያ***

- የዛሬው ታሪክ ኒቆዲሞስ ስለተባለ የአይሁድ ምሁር ነው፡፡
- በዚህም ከጌታችን ለመማር የነበረውን ፍቀር፣የተገለጠለትንም ምሥጢር እናያለን፡፡

***የክለሳ ጥያቄዎች***

1. ሽባውን ሰው ለማዳን የጣሩት ጓደኞቹ የገጠማቸውን ችግር እንዴት ፈቱ?
2. ገብርኄር ምን ማለት ነው?
3. ጌታችን ሲመጣ ምን ይጠይቀናል?

***ትምህርቱ***

- ወደ ክርስቶስ ሁሌ ማታ ማታ ለመማር የሚመጣ ኒቆዲሞስ የተባለ ሰው ነበር፤
- ስለክርስቶስ በጥልቀት ለማወቅና ከጌታችን መማርም ይወድ ነበር፡፡
- አንድ ቀንም ጌታችን ስለጥምቀት አስተማረው፡፡/ ጥምቀት ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ?/ከመምህር ጋር ተወያዩ፡፡/
- አንድ ቀን ኒቆዲሞስ በሌሊት መጥቶ *"መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንመጣህ እናውቃለን፡፡"* አለው፡፡
- ጌታችንም *"እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ የእግዚአብሔርን መንግሥት አያይም"* አለው፡፡
- ኒቆዲሞስም ተደንቆ *"ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል?ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን?"* አለ፡፡
- ጌታችንም *"ዳግመኛ መወለድ"* ምን ማለት እንደሆነ አብራራለት፡፡ *"ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም፡፡ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው÷ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው፡፡"* አለው፡፡
- ለዚህም ነው *"ጥምቀት ከውኃና ከመንፈስ ዳግመኛ መዋለድ ነው"* የምንለው ጌታችን ይሄን ምሥጢር ለኒቆዲሞስ የገለጠለት የመማር ፍቅር ስለነበረው ነው፤
- ልጆች መማር ትወዳላችሁ?በትምህርት ቤት፤በቤተክርስቲያን የሚሰጠውን ትምህርትስ በሚገባ ትከታተላላችሁ?

***መዝሙር***

እግዚአብሔር ይወዳናል ይጠብቀናል(2)
እርሱ ለኛ ደሙን ክሶልናል(2)

***ጥያቄዎች***

1. የመማር ፍቅር የነበረው የአይሁድ ሊቅ ማን ይባላል?

_______________________________________________

2. ለመማር የሚመጣውስ መቼ ነበር?

_______________________________________________

3. ጌታችን ለኒቆዲሞስ የገለጠለት ምሥጢር ምን ነበር?

_______________________________________________

4. ሰው ዳግመኛ የሚወለደው ከ__________ እና ______________ ነው፡፡

5. ጌታ ለኒቆዲሞስ ይህን የገለጠለት ለምንድነው?

_______________________________________________

**ይቆየን፡፡**